# የፌደራል ይቅርታ ቦርድ

## በፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚታዩ የሕግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 966/2015

ግንቦት 2015

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 966/2015

# በፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚታዩ የሕግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ መመሪያ

ለፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚቀርቡትን የይቅርታ ጥያቄዎች በተፋጠነ መልኩ ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻዎች አሟልተው መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች በግልጽ ማመላከት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

የፌደራል የህግ ታራሚዎች ይቅርታ አሰጣጥና አፈጻፀም ስነ-ሥርዓት አዋጅን ለማስፈጸም ወጥቶ የነበረዉ መመሪያ ዝርዝር መስፈርቶችን ያላስቀመጠና ግልጽ ባለመሆኑ፤

ታራሚዎችን የሚመለከት አስተያየት፣መረጃና ምስክርነት ከሚሰጡ ተቋማትና ግለሰቦች የሚፈለገውን ዝርዝር መረጃ በግልጽ ማስቀመጥና እንዲሁም የቦርድ አባላትም አዋጁን በአግባቡ ለማስፈፀም የሚያስችላቸውን ስነ-ሥርዓት መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

በይቅርታ አሰጣጥና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 አንቀጽ 28/2/ መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚታዩ የህግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 966/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ዉስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1) "**አዋጅ**" ማለት የይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 ነው፡፡
2) "**ቦርድ**" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት የተቋቋመ አካል ነው፡፡
3) "**ጽህፈት ቤት**" ማለት የይቅርታና ምህረት ቦርድ ጽ/ቤት ነው፡፡
4) "**መንግሥት**" ማለት የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ነው፡፡
5) **"የይቅርታ ጥያቄ"** ማለት በአዋጁ አንቀፅ 15፣ 16 እና 17 መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡
6) **"የቅርብ ዘመድ"** ማለት ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ለአካለ መጠን የደረሰ ልጅ፣ ባለቤት፣ ወንድም፣እህት፣አያት፣ አጎት ወይም አክስትነዉ፡፡
7) **"የፌደራል መንግስት ታራሚ"** ማለት በፌደራል ፍርድ ቤቶች ተፈርዶባቸው በፌደራል ማረሚያ ቤት የሚገኙ ወይም የክልል ፍ/ቤቶች የፌደራል ጉዳይ ሆኖ በውክልና የወሰኑባቸው በክልል ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ታራሚዎች ወይም በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የተፈረደባቸዉ ታራሚዎች ወይም በዝውውር ወደ ክልል ማረሚያ ቤቶች የተዘዋወሩ የፌደራል የህግ ታራሚዎች ናቸው፡፡
8) **"የክልል ይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤት"** ማለት በክልል ፍትህ ቢሮ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ህግበውስጥ አደረጃጀት በይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤት የተደራጀ ወይም የይቅርታን ጥያቄ የሚያስተናግድ አካል ነው፡፡
9) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፌደራል መንግስት ታራሚዎችና የሞት ፍርድ በሰጡ የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ አላማ የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብና አሰጣጥ ግልጽ፣ ፈጣን፣ ፍትሀዊና ወጥ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም የሚያስችል አሰራር እና መስፈርቶችን ለመደንገግ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ</u>

5. <u>የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1) በፌደራል ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ የህግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄያቸዉን ለጽህፈት ቤት የሚያቀርቡ ሲሆን በክልል የሚገኙ የፌደራል የህግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄያቸዉን በክልሉ ይቅርታ ቦርድ ጽሕፈት ቤት ወይም ስልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባሉ፡፡ ክልሎች በአዋጁ አንቀፅ 9/2/ ላይ በተሰጣቸዉ ዉክልና መሰረት የፌደራል ታራሚዎችንና የሞት ፍርደኞችን የይቅርታ ጥያቄ ሲያስተናግዱ ይህን መመሪያ መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በአዋጁ አንቀጽ 15/2/ መሰረት የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ማንኛውም ሰው ለይቅርታ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችልና ታራሚውን የሚመለከቱ መረጃዎች ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጁትን ቅጾች በትክክል መሙላት ይኖርበታል፡፡

3) ጽህፈት ቤቱ የተሞላዉን ቅጽ መሰረት በማድረግ ከማረሚያ ቤት ማስረጃዎች ተሟልተዉ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

4) በአዋጁ አንቀጽ 15/4/ መሰረት በፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን፣ በክልል ይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤቶች ወይም በፍትህ ሚኒስቴር ተጠንቶ በየሶስት ወሩ እና እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛዉም ጊዜ በሰንጠረዥ ለታራሚዎች ይቅርታ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡

5) በአዋጁ አንቀጽ 16(1) ላይ የተዘረዘረዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች ይቅርታ ጠያቂዉ ማቅረብ አለበት፡

ሀ/ ማረሚያ ቤት የገባበት ቀን፣ ከማረሚያ ቤት ዉጭ የታሰረዉ ጊዜ፣እና በማረሚያ ቤትና ከማረሚያ ቤት ውጭ የቆይታ ጊዜ፤

ለ/ በአዋጁ አንቀጽ 16(1) (ረ) እንደተጠበቀ ሆኖ ማረሚያ ቤቱ ታራሚዉ ይቅርታ ሊደረግለት አይገባም ብሎ ካመነ ምክንያቱን፤

ሐ/ የህግ ታራሚዉ የይቅርታ ጥያቄዉን መቀበሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

6) በአዋጁ አንቀጽ 17/1/ለ/ እና /ሐ/ መሰረት የይቅርታ ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜን ሳይጠብቅ የሚቀርብ አቤቱታ እና በመመሪያዉ የተዘረዘሩትን መስፈርቶችባያሟላም የታራሚዉ መፈታት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በጉልህ ይረዳል ተብሎ በቦርዱ ሰብሳቢ ከታመነ የታራሚዉ አቤቱታ ወይም ጥያቄ ለቦርድ እንዲቀርብ ለጽህፈት ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

7) በዚሁ አንቀጽ 5 በተገለጸዉ ሁኔታ አቤቱታ ወይም የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርብ በፌደራልም ይሁን በክልል የሚገኝ የፌደራል ታራሚ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6/5/ ስር የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 5 ከተገለጸዉ ዉጪ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት መስፈርቶች ካልተሟሉ ጽህፈት ቤቱ የይቅርታ ጥያቄዉን ለቦርድ አያቀርብም፡፡

## 6. <u>በክልል ማረሚያ ቤት ከሚገኙ የፌደራል ታራሚዎች በድጋሜ ስለሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎች</u>

በክልል የሚገኝ የፌደራል የህግ ታራሚ የይቅርታ ጥያቄዉ በክልል ይቅርታ ቦርድ በአዎንታዊ አስተያየት ተሰጥቶት ለመጨረሻ የዉሳኔ ሀሳብ በፌደራል ይቅርታ ቦርድ ታይቶ ከፊል ይቅርታ ተሰጥቶት ወይም ዉድቅ ተደርጎበት በድጋሚ የሚያቀርብ ከሆነ በክልሉ ይቅርታ ቦርድ በድጋሚ መታየት ሳይጠበቅበት ታራሚዉ ከሚገኝበት ማረሚያ ቤት የታራሚዉን የማረሚያ ቤት ቆይታ ባህሪ የሚገልፅ እንዲሁም በይቅርታ ቢፈታ “እንደግፋለን ወይም አንደግፍም” የሚለውን አስተያየት ከእነምክንያቱ ተካትቶ በክልሉ ይቅርታ ቦርድ ጽህፈት ቤት በኩል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 7. የይቅርታ ጠያቂ መልካም ጸባይና ሥነ-ምግባር

1) ቦርዱ ይቅርታ በሚሰጥበት ወቅት የይቅርታ ጠያቂዉ በማረሚያ ቤት ቆይታዉ ወቅት ያሳየዉን መልካም ጸባይና ሥነ-ምግባር ለመወሰን የወንጀሉን ክብደትና የይቅርታ ጠያቂዉን የማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜ ከግምት ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አፈጻጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ/ የፍርድ ልኩ ሃያ አምስት አመትና ከዛ በታች የሆነ የህግ ታራሚ የፍርዱን 1/3ኛ ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር፤

ለ/ የእድሜ ልክ ፍርደኛ የፍርዱን 12 ዓመት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር፤

ሐ. የሞት ፍርድ ሲሆን ፍርዱ ሳይፈጸም 15 ዓመት በማረሚያ ቤት ከቆየ በእነዚህ አመታት ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር፤

መ. በሚከተሉት ወንጀሎች ተከሰዉ ጥፋተኛ የተባሉ የህግ ታራሚዎች ከወንጀሎቹ ክብደትና በሃገር ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት ጉዳት አንጻር 1/2ኛ ጊዜ ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር፡

i. ሙስና፤

ii. በሰዉ መነገድ እና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር፤

iii. በሕገወጥ የጦር መሣሪያ ንግድና ዝውውር፤

iv. ሽብርተኝነት፤

v. የሃሰት ገንዘብ መሥራት ወይም ማዘዋወር፤

vi. መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም እጾችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም፤

vii. የግብረሰዶምና ለክብረ ንፅህና ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶች፤

viii. በሴቶች ወይም በህጻናት ላይ ታስቦ የሚፈጸም ግድያ ፣ የግድያ ሙከራ እና ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጠለፋ፤ የግብረ ስጋ ድፍረት ወንጀል፤

ix. በመብራት፣ ውሀ፣ ቴሌኮሙዩኒኬሽን፣ የባቡር መስመሮች፣ ድልድዮች እና በሌሎች የመንግስት መሰረተ ልማቶች ላይ የሚፈጸም ወንጀል፤

X. ከባድ የሃገር ክህደት ወንጀል፤

xi. የታክስ ስወራና ማጭበርበር ወንጀሎች፤

xii. የኮንትሮባንድ ወንጀሎች፡፡

3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና፣ በታክስ ስወራና ማጭበርበር ወንጀሎች ለደረሰዉ ጉዳት ተመጣጣኝ ማካካሻ ለመንግስት የከፈለና የፍርዱን 1/3ኛ ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር ከግምት ዉስጥ ይገባል፡፡

4) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሴቶች ወይም በህጻናት ላይ ታስቦ የሚፈጸም ግድያ ፣ የግድያ ሙከራ እና ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጠለፋ፣የግብረ ስጋ ድፍረት፣ ለክብረ ንፅህና ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶችን እና የግብረሰዶም ወንጀሎችን የፈፀመ ታራሚ ለደረሰዉ ጉዳት የሞራል ካሳ የከፈለና የፍርዱን 1/3ኛ ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳየዉን መልካም ሥነ-ምግባር፤

5) እድሜዋ ከ55 ዓመት በላይ የሆነች ሴት ታራሚ፣ ወይም እድሜው ከ60 ዓመት በላይ የሆነ ወንድ ታራሚ በፈጸሙት ወንጀል ሶስት አመት እና ከዛ በታች የተፈረደባቸው እንደሆነ 1/4ኛ ቅጣታቸዉን ሲፈፀሙ በማረሚያ ቤት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳዩት መልካም ሥነ-ምግባር፤

6) በፈጸሙት ወንጀል ሶስት አመት እና ከዛ በታች የተፈረደባቸው እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የህግ ታራሚዎች 1/4ኛ ቅጣታቸዉን ሲፈፀሙ በማረሚያ ቤት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳዩት መልካም ሥነ-ምግባር፤

7) በፈጸሙት ወንጀል 3 አመትና ከዛ በታች ተፈርዶባቸዉ እድሜዉ ሁለት አመትና ከዛ በታች የሆነ ህጻን ልጅ ይዘው ወደ ማረሚያ ቤት የገቡ የህግ ታራሚዎች ወይም

ነፍሰ ጡር የሆኑ ታራሚዎች 1/4ኛ ቅጣታቸዉን ሲፈፀሙ በማረሚያ ቤት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳዩት መልካም ሥነ-ምግባር፤

8) በፈጸሙት ወንጀል 3 ዓመትና ከዛ በታች ተፈርዶባቸዉ አካል ጉዳተኛ የሆኑ የህግ ታራሚዎች1/4ኛ ቅጣታቸዉን ሲፈጸሙ በማረሚያ ቤት ቆይታ ጊዜ ዉስጥ ያሳዩት መልካም ሥነ-ምግባር፤

9) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርቡ ማንኛዉም የይቅርታ ጥያቄ ይቅርታ ጠያቂዉ በማረሚያ ቤት ቆይታዉ የሙያ ወይም ሌሎች የማህበራዊ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ሰነድ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት፡፡

8. <u>በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎች</u>

ከዚህ በታች የሚከተሉት ታራሚዎች በልዩ ሁኔታ በማንኛዉም ጊዜ የይቅርታ ጥያቄ ለጽህፈት ቤቱ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡

1) በተከሰሰበት ወንጀል አምስት አመት እና ከዛ በታች የተፈረደበት ታራሚ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ዉጤት ካሟላ፤

2) በከባድ በሽታ ተይዞ ለመታረም አስቸጋሪ መሆኑ በማረሚያ ቤት የሃኪሞች ቦርድ የተረጋገጠለት ታራሚ፤

3) ከታራሚዋ ወይም ከታራሚዉ ጋር አብሯት የሚኖረው እና ልጇ ወይም ልጁ የሆነው ህጻን የጤና ችግር ያጋጠመው በመሆኑ ምክንያት ለእርምትና ለአያያዝ አስቸጋሪ መሆኑ እና ስለህጻኑ የጤና ችግር በማረሚያ ቤት የሃኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ ያቀረበች ወይም ያቀረበ የህግ ታራሚ፤

4) ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የጤና ችግር ያጋጠማት እና በማረሚያ ቤት የሃኪሞች ቦርድ ማስረጃ ማቅረብ የምትችል ታራሚ፡፡

9. <u>የሞት ፍርድ የተወሰነባቸውን ታራሚዎች በተመለከተ</u>

1) የሞት ፍርደኛ በአዋጁ አንቀፅ 15(2) ከሚቀርበዉ የይቅርታ ማመልከቻ በተጨማሪ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች በራሳቸው ተነሳሽነት የይቅርታ መስፈርቱን ለሚያሟሉ የህግ ታራሚዎችን የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፤

2) በሞት ፍርድ ላይ የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብ በዚሁ መመሪያ በአንቀጽ 6/5/ የተጠቀሱት ማስረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፤

3) የክልል ይቅርታ ቦርድ ወይም የይቅርታን ጉዳይ የሚመለከት አካል፣ የፌደራል ማረሚያ ቤት ለሞት ፍርደኞች የይቅርታ ጥያቄ ሲያቀርብ በግልጽ ይቅርታን መደገፉን ወይም አለመደገፉን ከእነምክንያቱ መግለጽ አለበት፡፡

10. <u>ስለ እርቅ ማስረጃ</u>

1) በሚከተሉትን ወንጀሎች ወይም ሌሎች እርቅ መፈጸም በሚገባቸዉ ወንጀሎች የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት በማረሚያ ቤት የሚገኝ ታራሚ ከሚያቀርበው የይቅርታ ጥያቄ ጋር መፀፀቱን የሚገልጽ የእርቅ ማስረጃ ወይም ለመታረቅ ያደረገውን ተገቢዉን ጥረት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡

ሀ. የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል፤

ለ. ግድያ እና የግድያ ሙከራ ወንጀል፡፡

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁኔታዉ ሙሉ በሙሉ ለመታረቅ የማይቻል ከሆነ በቦርዱ ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ግምት ዉስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

3) የእርቅ ማስረጃው ፍርድ ቤት ያልቀረበ ከሆነ፤ ወይም የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተደረገ የእርቅ ማስረጃ ከሆነ፤ ወይም ማስረጃው አጠራጣሪ ከሆነ የፌደራል ይቅርታ ቦርድ ፅህፈት ቤት ተጎጂው ወይም የሟች የቅርብ ቤተሰብ የእርቁን ትክክለኛነት አመች በሚለዉ መንገድ እንዲያረጋግጡ ያደርጋል፡፡

4) ቦርዱ የቀረበዉን የእርቅ ማስረጃ ወይም ለመታረቅ ያደረገዉን ጥረት አሳማኝነትና ተያያዥ ማስረጃዎችን የይቅርታ ጥያቄውን ሲመረምር በመስፈርትነት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

11. <u>የእርቅ ፈጻሚ ወገኖች</u>

1) የግል ተበዳይ ባለባቸዉ ወንጀሎች ላይ ከግል ተበዳይ ጋር እርቅ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የግል ተበዳይ በህይወት የሌለ እንደሆነ እርቁ ከተበዳይ የትዳር አጋር፣ ልጅ/ልጆች፣ አባትና እናት እንዲሁም እህትና ወንድም ጋር መፈፀም ይኖርበታል፡፡

3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ከተዘረዘሩት አካላት ጋር በከፊልም ሆነ በሙሉ እርቅ ያልፈጸመ እንደሆነ ያልፈጸመበትን ምክንያት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

12. <u>ስለ ይቅርታ አሰጣጥ</u>

በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ለተገኘ ታራሚ ቦርዱ በይቅርታ እንዲፈታ የዉሳኔ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. <u>ተጠያቂነት</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ የእርቅ ማስረጃ፣ የህክምና ማስረጃ እና ሌሎች ሰነዶችን ያቀረበና የሰጠ ማንኛዉም አካል አግባብነት ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

14. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1) የፌዴራል ይቅርታ ቦርድ መመሪያ ቁጥር 1/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2) የዚህን መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

15. <u>መመሪያዉን ስለማሻሻል</u>

ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘዉ ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሻል ይችላል፡፡

16. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ቁጥር ተሰጥቶት በድሕረ ገጽ ላይ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የፌደራል ይቅርታ ቦርድ**

**18 ግንቦት 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**